# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# የአካባቢ ጥበቃ እና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን

## የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አፈጻጸም

## መመሪያ ቁጥር አንድ/፩//2013

መጋቢት፣ 2013 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## መግቢያ

የአዲስ አበባ ከተማ የሀገራችን ዋና መዲና የአፍሪካ መቀመጫ የአለም አቀፍ ድርጅቶችና ኤምባሲዎች የሚገኙበት ከተማ እንደመሆኗ መጠን በዓለም ላይ የከተሞች እድገት በመጠንም ሆነ በቁጥር እጅግ ፈጣን እየሆነ መጥቷል፡፡ በመሆኑም የኢኮኖሚና የማህበራዊ አዉታሮች እድገትም በአብዛኛዉ በከተሞች አካባቢ ጎልቶና ተከማችቶ ይታያል፡፡ የከተሞች የህዝብ ብዛት እድገትም ከጊዜ ወደ ጊዜ በፍጥነት እየጨመረ ይገኛል፡፡ከዚህ ጋር ተያይዞ የመኖሪያ ቤት እጥረትና የአካባቢ ብክለት በከተሞች አካባቢ እጅግ የከፋ ችግር ሆኖ ይገኛል፡፡ በአገራችን ከሚከናወኑ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ተቋሞች መካከል አብዛኞቹ በከተሞች አካባቢ የሚገኙ ናቸው፡፡

በመሆኑም እነዚህን ችግሮች ከወዲሁ ችግሮች ለመግታት በፌደራል መንግስት ከወጡት የአካባቢ ህጎች በተጨማሪ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደረም ከከተማዋ ተጨባጭ ሆኔታ በመነሳት የአካካቢ ደህንነት ላይ ያተኮረ በርካታ ደንቦችን አዉጥቷል፡፡ ከነዚህምዉስጥ አንዱ የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር ደንብ ቁጥር 25/2000፣300/1995፣513/2000፣109/210እና1075/2010ደንብእና አዋጅ ለመትግበር ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህን የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አፈጻጸም መመሪያ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን አዉጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**1.1.አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ እና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን የአካባቢ ብክለት ቁጥትር አፈጻጸም መመሪያ ቁጥ ርአንድ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

1.2. "**ትርጓሜ**"፡-የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የማይሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ዉስጥ

2.1.1. "**እስተዳደር**"፡- ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነዉ፡፡

2.1.2. "**ከተማ**"፡- ማለት አዲስ አአበባ ነዉ፡፡

2.1.3. "**ኮሚሽን**" ፡- ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃና አርንጓዴ ልማት ኮሚሽን ከማዕከል እስከ ወረዳ ያለዉን መዋቅር ያካተተ ነዉ፡፡

2.1.4. "**እካባቢ**"፡- ማለት በመሬት ፤በከባቢ አየር፤በአየር ሁኔታና በአየር ንብረት በዉሃ በህያዋን ፤ በድምጽ፤ በሽታ፤ በጣዕም በማህበራዊ ጉዳዮች እና በስነ ዉበት ሳይወሰን በተፈጥረዊ ሁኔታዎች ወይም በሰዉ አማካነኝነት ተሻሽለዉ ወይም ተለውጠው የሚገኙ ነገሮች በጠቅላላ ያሉበት ቦታ እንዲሁም መጠናቸዉ ወይም ሁኔታቸዉ የሰዉ ወይም የሌሎች ሕዋን በነ ሆነታና የሚነኩ መስተጋብሮቻቸዉ ድምር ነዉ፡፡

2.1.5. "**በካይ**" ማለት ፍሳሽ፣ ጠጣር ወይም ጋዝ የሆነ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ፡

**ሀ**.ያረፈበትን የአካባቢ ክፍል ጥራት በመለወጥ ጠቀሜታ የመስጠት አቅሙን የሚያጓድል፤

**ለ**. በሰው ጤና ወይም በሌሎች ህያዋን ላይ ጉዳት የሚያደርስ ወይም ሊያደርስ የሚችል መርዝን፣ ክርፋትን፣ ጨረርን፣ ድምጽን፣ ንዝረትን፣ ሙቀትን ወይም ሌላ ክስተትን የሚያመነጭ ማንኛውም ነገር ነው ፡፡

2.1.6. "**ቆሻሻ**"፡-ማለት ተጠቅመንበት ያለፈ ሆኖ በአካባቢ ወይም በሰው ደኅንነት ወይም ጤና ላይ ጉዳት ያደርሳል ተብሎ የሚታመን ማንኛውም ነገር ነው፡፡

2.1.. **“ፆታ አገላለጽ“፡-** በዚህ መመርያ ውስጥ በልዩ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር በወንድ ፆታ የተገለጹ አገላለጾች ለሴት ጾታም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

2.1.18. **“አደገኛ ቆሻሻ”፡-** ማለት ተፈላጊነት የሌለው ሆኖ በአካባቢው ወይንም በሰው ድህንነት ወይም ጤና ላይ ጉዳት ያደርሳል ተብሎ የሚታመን ማንኛውም ነገር ነው ፡፡

2.1.19. **“አደገኛ ነገር”፡-** ማለት በሰው ጤና ወይም በአካባቢ ላይ ጉዳት የሚያደርስ ጠጣር፣ፈሳሽ ወይም ረቂቅ ህዋስ ነው፡፡

2.1.20. **“መልቀቅ”፡-** ማለት በውል ታስቦም ይሁን ሳይታሰብ በካይን ወደ ማንኛውም የአካባቢ ክፍል መጨመር ነው፡፡

2.1.21. **“አስወጋጅ”፡-** ማለት በአደገኛ ቆሻሻ ማስወገድ ስራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ማለት ነው፡፡

2.1.22. **“አመንጪ”፡-** ማለት ማንኛውም ቆሻሻ የሚያመነጪ ሰው ወይንም ድርጅት ሲሆን አመንጪው ባልታወቀበት ሁኔታ አደገኛ ቆሻሻውን በማወቅ ወይንም ባለማወቅ በይዞታው ስር አድርጎ የሚገኝ ነው ፡፡

2.1.23. **“ጉድፍ”፡-** ማለት የጠትሙስ ስባሪ፣ የብረት ፣ የሲጋራ፣ የፕላስቲክ ወይም የወረቀት ቁርጥራጭን፣ የጨርቅ እራፊን፣ የምግብ ትራፊን እና የእፅዋት ቅሪትን ጨምሮ የተጣለበትን ቦታ ውበት ወይም ንፅህና የሚያሳጣ የሚጠቅምም ይሁን የማጠቅምም ማንኛውም ነገር ነው ፡፡

3. **አላማ**

- የአዲስ አበባ ከተማ ግልጽ የስራን መመሪያ በማውጣት የአካባቢን ብክለት አደጋን በተሟላ ሁኔታ በመጠበቅ የኗሪዎቿን በንጽህና ባልተበከለ አካባቢ ህገ- መንግስታዊ መብትን በማስከበር ከተማዋን ምቹና ተስማሚ የመኖሪያና የስራ አካባቢ ማድረግ፤
- የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር ተግባርን ፍታዊና ተጠያቂነት ያለበት ግልጽና ቀልጣፋ አሰራር በመከተል አስቀድሞ በመከላከል ላይ ማተኮርና ተበክሎ ሲገኝ መርህን በመከተል በካዩች ባደረሱት ብክለት ተጠያቂ በማድረግ በካዩ ያደረሰውን ጉዳት ወደ ቀድሞ ሁኔታ የሚመለስበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው፡፡

4. **የተፍጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ አካባቢ ሊበክሉ  የሚችሉ ነገሮችን በማመንጨት ወይም በመልቀቅ በአካባቢ ደህንነት ላይ ብክለት እና ሌሎች አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ሊያስከትሉ የሚችሉና ይችላሉ ተብለው በሚገመተ ሁሉም ፋብሪካዎች፤ አምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት  ላይ  በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## 1.ስለ አካባቢ ደረጃዎች እና ብክለት ቁጥጥር

### 1.1. ስለ አካባቢ ደረጃዎች

የአካባቢ ደረጃዎች፣ በጥራት ደረጃዎች፣ በቆሻሻ ማስወገጃ ደረጃ፣ በአደገኛ ነገሮች የአመራረት እና አያያዝ ሂደቶች እና በመሳሰሉት ይገለፃል፡፡ አስተዳደሩ የራሱን አካባቢ ደረጃ እስኪያወጣ ድረስ በፌደራል መንግስት አግባብነት ባላቸው መስሪያ ቤቶች የወጡ የአካባቢ ደረጃዎችን ይጠቀማል፡፡ ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ደግሞ አግባብነት ባላቸው ዓለማቀፍ ህጎች፣ የወጡ የአካባቢ ደረጃዎች እንደ አግባብነታቸው መከበራቸውን ኮሚሽኑ መቆጣጠር አለበት፡፡ አስተዳደሩ የራሱን አካባቢ ደረጃ እስኪያወጣ ድረስ በፌደራል መንግስት አግባብነት ባላቸው መስሪያ ቤቶች የወጡ የአካባቢ ደረጃዎችን ይጠቀማል፡፡ ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ደግሞ አግባብነት ባላቸው ዓለማቀፍ ህጎች፣ የወጡ የአካባቢ ደረጃዎች እንደ አግባብነታቸው መከበራቸውን ኮሚሽኑ መቆጣጠር አለበት፡፡

ሀ. ለሰው ልጅ ጤንነት ስለአካባቢ ደህንነት እንዲሁም ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች የሚውል አግባብ ያለው የውሃ ጥራት፤

ለ. ለሰው ልጅ ጤንነት ህይወትና ጤንነት፤ ለእንስሳት ለተክሎች ተስማሚ የሆነ የአየር ጥራት ደረጃና ወደ አፈር የሚጨመሩ ኬሚካሎች አይነትና መጠን የሚወስኑ የአፈር ደህንነትን የሚጠብቅ የአፈር ጥራት ደረጃ፤

ሐ. ወደ አፈር የሚጨመሩ ኬሚካሎች አይነትና መጠን የሚወስኑ የአፈር ደህንነት የሚጠብቅ የአፈር ጥራት፤

መ. ለኢንዱስትሪ፤ ለግንባታ ቦታዎች፤ ለተሽከርካሪዎች ለአውሮፕላኖች፤ ለልዩ

ልዩ መሳሪያዎች ለንግድ ተቋማትና ለሌሎች ድምጽ አመንጭ ነገሮች የድምጽ መጠን ደረጃ፤

ሠ. የአደገኛ ነገሮች አመራረትና አያያዝ፤ አጠቃቀም ከቦታ ቦታ የማጓጓዝ የብቃት ደረጃ፤

ረ. ወደ ውሃ አካላት ወደፍሳሽ መስመሮች፤ ወደ ከተማ ፍሳሽ ማጣሪያ መስመር፤ እንዲሁም ወደ ግለሰብ ፍሳሽ ማጣሪያ መስመር የሚለቀቁ የፍሳሽ ደረጃ፤

ሰ. ለአካባቢ ደህንነት ለሰው ልጅ ጤንነት የሚስማማ የሽታ፤ የእይታ መጠን ደረጃ

### 1.2. የውሃ ጥራት ደረጃ

ለቤት ውስጥ አገልግሎት፤ ለኢንዱስትሪ ለመዝናኛ እና እንደስፈላጊነቱ ለሌሎች ተግባሮች ጥቅም ላይ የሚውል ውሃን የሚመለከት ይሆናል፡፡

### 1.3. የአየር የጥራት ደረጃ

ሀ. ለሰው ልጅ ህይወትና ጤንነት፤ አስፈላጊ የሆነ ዝቅተኛ ሆነ የአየር ጥራት ደረጃ ፤

ለ. ለእንስሳት ለተክሎች እንዲሁም በንብረት ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል የበካይ ነገሮች መጠንን፤

### 1.4. የፍሳሽ ለአካባቢ ተስማሚ ደረጃ

ሀ. ወደ ውሃ ወይመር ወደ መሬት የሚለቀቀው፤ የሚደፋው ፤ የሚቀበረው ወይም ወደ ፍሳሽ መስመር እንዲገባ የሚፈቀደው ፍሳሽ፤

ለ. በፍሳሽ መስመር በፍሳሽ ማጣሪ ጣቢያ ከተጣራ በኋላ ወደ ውኃ ወይም መሬት የሚለቀቅ ፍሳሽ፤

### 1.5. ፍሳሽ ወደ ፍሳሽ መስመር ስለመልቀቅ

ማንኛውንም ፍሳሽ ወደ ፍሳሽ መስመር ለመልቀቅ የሚፈልግ ሰው በህግ ስልጣን ከተሰጠው አካል ፈቃድ ካልተሰጠው በስተቀር የፍሳሽ መስመሩን መጠቀም አይችልም፡፡ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩትን የፍሳሽ የጥራት ደረጃዎች የማያሟላ ፍሳሽ ወይም ሌላ ነገር ወደ ፍሳሽ መስመር መልቀቅ ወይ ማስገባት እንዲለቀቅ ወይም እንዲገባ ማድረግ ይከለክላል ፡፡

ሀ. በፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ ላይ ሊጣራ የሚችል ወይም የማጣሪያ ጣቢያውን ስራ የሚያውክ ወይም ማጣሪያ ሂደት ላይ ችግር የሚፈጥር ፍሳሽ፤

ለ. ከፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ ተጣርቶ የሚወጣ ፍሳሽ የጥራት ደረጃ በመቀነስ

ወይም በማጓደል በመንስት የወጣውን ደረጃ እንዲያሟላ ያደርጋል ተብሎ የሚገመት ፍሳሽ፣

ሐ. በራሱ ወይም ከሌላ ንጥረ ነገር ጋር በማዋሀድ መርዛማ ኬሚካል በማመንጨት በመስመር ጥገና ላይ በሚሰሩ ማንሆል ውስጥ ገብተው በሚሰሩ ሰራተኞች ላይ ጉዳት ያደርሳል ተብሎ የሚገመት ፍሳሽ፣በቴክኖሎጅ በመጠቀም ማስወገድ አለበት

መ. በራሱ ወይም ከሌላ ንጥረ ነገር ጋር በማዋሀድ በፍሳሽ መስመር ወይም በማጣሪያ ጣቢያ ወይም የተጣራው ፍሳሽ በሚለቀቅበት ውሃ እና አፈር ላይ ጉዳት ያደርሳል ተብሎ የሚገመት ፍሳሽ፣ከሆነ ጉዳት በማየደረስ አሰራር ተጠንቶ መወገድ ይገባዋል፡፡

ሠ. የፍሳሽ ሙቀት ፍሳሽ መስመሩ ጋር በሚገናኝበት ቦታ ላይ ሲለካ ከመቶ ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ የበለጠ ፍሳሽ፣ መለቀቅ የለበትም

ረ. ፍሳሽ ፒኤች ከ5.5 ከአነሰ ወይም ከ10.0 የሚበልጥ ከሆነ፣

ሰ. በፍሳሽ መስመር ውስጥ የሚቀጣጠል ወይም የሚፈነዳ ወይም መርዛማና አደገኛ ጋዝ ወይም ትነት ያመነጫል ተብሎ የሚገመት፣

ሸ. ከአንድ መቶ ድግሪ ሴንቲ ግሬድ በታች የሆነ ሙቀት ሊተኑ የያዙ ነገሮች በውስጡ የያዘ ፍሳሽ ፣

ቀ. ዘይት፣ ጨዋማ፣ የተቀጣጠለ የሞተር ዘይት ወይም ሳሙና ነክ የሆኑ እና ሌሎች መስመሩን ሊዘጉ የሚችሉ ወይም ማጣሪያ ጣቢያውን በትክክል እንዳይሰራ ሊያደርጉ የሚችሉ በውስጡ የያዘ ፍሳሽ፣

# ክፍል ሶስት

## 2. የበካይ ነገሮች አያያዝና አወጋገድ ስርዓት

### 2.1. ደረቅ ቆሻሻ

ሀ.ደረቅ ቆሻሻ ከሰው ወይም ከእንስሳት የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ የሚመነጭ ወይም የሚፈጠር ሲሆን አያስፈልጉም፣ አይጠቅሙም ወይም አገልግሎታቸውን ጨርሰዋል ተብለው የሚጣሉ ነገሮች ስብስብ ነው፡፡

ለ. በይዘቱም ከተለያዩ መኖሪያ ቤቶች፣ ከንግድ ሱቆች እንዲሁም የህዝብ አገልግሎት ከሚሰጡ ተቋማት ከሚወጡ ቆሻሻዎች ማዘጋጃ-ቤታዊ ቆሻሻዎች ጀምሮ የግብር ውጤት የፋብሪካ እና የማዕድን ደረቅ ቆሻሻዎችን እና ተረፈ ምርቶችን ያጠቃልላል፡፡

ሐ. ደረቅ ቆሻሻ የሚያካትታቸው ከመኖሪያ ቤትና ከተለያዩ ተቋማት የሚወጡ ተረፈ ምርቶች፣ የጠርሙስ ስብርባሪ፣ አገልግሎቱን የጨረሱ ጣሳ፣ ፕላስቲክና የፕላስቲክ ከረጢቶች፣ ያገለገለ የተሽከርካሪ ጎማ፣ የግንባታ እና የህንጻ ፍርስራሾች እና ሌሎቹንም ያካትታል፡፡

### 2.2. ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ

ደረቅ ቆሻሻን በመሰብሰብ ፣በማጓጓዝ፣ በጥቅም ላይ በማዋል ወይም በማስወገድ ተግባር ላይ የሚሰማራ ማንኛውም ሰው ከሚመለከተው መ/ቤት በቅድሚያ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

ሀ. ማንኛውም ቆሻሻ የሚያመነጭ ሰው ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀ ቦታ ከሚመለከተው አካል በሚሰጠው ፈቃድና የአወጋገድ ዘዴ መሰረት ማስወገድ አለበት፡፡

ለ. ማንኛውም ቆሻሻ የሚያመነጭ ሰው /ተቋም፣ አደገኛ ቁሶችን ወይም—ቆሻሻ ከማስወደጉ በፊት በተገቢ ሁኔታ በተዘጋጀና አካባቢን ወይም የአካባቢ አካላትን በማይበክል ሁኔታ ማስቀመጥ አለበት፡፡

መ. ማንኛውም ከኢንዱስትሪ የሚወገዱ ደረቅ ቆሻሻዎችን ወይም ተረፈ ምርቶችን ከአደገኛ ኬሚካል ጋር ቀላቅሎ ማስወገድ የለበትም፣

ሠ. ማንኛውም የጤና ተቋም በሽታ አስተላላፊ ተህዋስያን ወይም ኬሚካል ጋር ንክኪ ያለውን ደረቅ ቆሻሻ ለዚሁ ተብሎ በአግባቡ በተዘጋጀ እና ደረጃዉን በጠበቀ ማቃጠያ ብቻ ማቃጠል አለበት፡፡

ረ. ማንኛውንም ቆሻሻ ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ሳይዝ ቆሻሻን ማመንጨት፣ ማስቀመጥ፣ ማከማቸት፣ ማጓጓዝ፣ ማምከን ወይም ማስወገድ የተከለከለ ነው፡፡

ሰ. ማንኛውም ሰው በተቻለ መጠን አነስተኛ ቆሻሻ የሚፈጥር የአጠቃቀም ዘዴ ወይም የአመራረት ሂደት መከተል አለበት፣

ቀ. ማንኛውም ሰው ከተፈጠረው ቆሻሻ ተመልሶ በጥቅም ላይ ሊውል የሚችለውን ለይቶ ጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ አለበት፣

በ. ማንኛውም ሰው መወገድ ያለባቸውን የቆሻሻ አይነቶችን አነስተኛ ቦታ እንዲይዙ አድርጎ ማጨቅና ሊያስከትሉት የሚችሉትን ጉዳት ስነ-ህይወታዊ ወይም ኬሚካላዊ በሆነ መንገድ ማስቀረትና ጥቅም ላይ ማዋል አለበት፣

ተ. ማንኛውም ሰው ደረቅ ቆሻሻ ባልተፈቀዱ ቦታዎች ማለትም በየመንደሩ፣ በየመንገዱ፣ በጎርፍ መውረጃ ቱቦዎች ፣በፓርኮች፣ በአውቶቡስ ፌርማታዎች፣ በስፖርት ሜዳ፣ በወንዞችና በወንዝ ዳርቻዎች ወዘተ መጣል የለበትም፣

ቸ. ማንኛውም የአትክልትና ፍራፍሬ ንግድ ላይ የተሰማራ ሰው ተረፈ ምርቶችን ለጤና ወይም ለአካባቢ ጎጂ ባልሆነ ሁኔታና ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ የተለየ ማጠራቀሚያ ዕቃ ማከማቸት አለበት ይህ አማራጭ ከሌለ በራሱ ሃላፊነት ወደተፈቀደ ማስወገጃ ሥፍራ ማድረስ ወይም ወደቀልዝነት የሚለወጥበትን መንገድ ማመቻቸት አለበት

ኀ. ከግንባታና ልዩ ልዩ ሥራዎች ሂደት የሚመነጭ አፈር ፍርስራሽና ሌሎችምም መሰል አላስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ባልተፈቀዱ ቦታዎች መድፋት የተከለከለ ነው፡፡

ነ. ማንኛውም የቆርቆሮ ጣሳ ወይም ጠርሙስ አምራች ወይም አስመጪ ጣሳው ወይም ጠርሙሱ ከአገልግሎት በኋላ መልሶ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ዘዴ መዘርጋትና መተግበር አለበት፡፡

ኘ. ውፍረቱ 0.03 ሚ.ሜ እና ከዚያ በታች የሆነ በስብሶ ከአፈር ጋር የማይዋሃድ ፕላስቲክ ማምረትም ሆነ መሸጥ የተከለከለ ነው፡፡

### 2.3.ስለ አደገኛ ቆሻሻ

### 2.3.1. የአደገኛ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ ዝግጅት

ሀ. በአዲስ አበባ የሚገኝ እያንዳንዱ ወረዳ ህብረተሰቡን ባሳተፈ መልኩ የወረዳውን የአደገኛ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ ማዘጋጀትና መተግበር አለበት፣

ለ. እያንደንዱ ወረዳ የአደገኛ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ማዘጋጀት አለበት፣

ሐ. እያንዳንዱ ክ/ከተማ በውስጣቸው የሚገኙትን ወረዳዎች ባዘጋጁት ዕቅድና ዘገባ ላይ ተመስርቶ አጠቃላይ የክ/ከተማውን ዕቅድና ዘገባ ማጠናቀር አለበት፡፡

## 2.4. ፍሳሽ ቆሻሻ

### 2.4.1. ከመኖሪያ ቤት የሚወጣ ፍሳሽ ቆሻሻ

ከመኖሪያ ቤት የሚወጣ ፍሳሽ ማለት የልብስ እጣቢ፣ የመታጠቢያ ቤት እጣቢ፣ ከምግብ ማብሰያ አካባቢዎች የሚወጣ እጣቢ፣ የሽንት ቤት ፍሳሽ የመሳሰሉትን ፍሳሾች ይጨምራል፡፡ እነዚህ ፍሳሾች በሴፕቴክ ታንክ ተጠራቅመው ሴፕቲክ ታንኩ በሚሞላበት ወቅት መመጠጥና ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ባዘጋቸው የፍሳሽ ማጠሪያ ጣቢያ ሊጣራ ይገባዋል፡፡ ከላይ የተዘረዘሩትን የፍሳሽ አይነቶች ከሴፕቴክ ታንክ ውጭ በቱቦ ከግቢ ውጭ በማስወጣት ወደ መንገድና ወደ አካባቢው መልቀቅ የተከለከለ ነው፡፡ በመንገድ ዳር የተሰራው ቱቦ አገልግሎቱ የጎርፍ ውሃ ወይም የዝናብ ውሃ ማስተላለፊያ ስለሆነ ይህን ቱቦ ለሌሎች ፍሳሾች ማስተላለፊያነት መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ኬሚካል ነክ ፍሳሾችን ተገቢውን የማከሚያ ዘዴ ሳይጠቀሙ ወደ ጎርፍ ማስወገጃ መልቀቅ የተከለከለ ነው፡፡

### 2.4.2. ከኢንዱስትሪ የሚወጣ ፍሳሽ ቆሻሻ

ከማንኛውም ኢንዱስትሪ የሚለቀቁ ፍሳሽ ቆሻሻዎች ተገቢው ህክምና ተደርጎላቸው አካባቢ ሊሸከመው የሚችለው ደረጃ ላይ ሳይደርሱ በአቅራቢያ ወደሚገኘው የፍሳሽ ማስተላለፊያ ቱቦ ወይም ወደ ማንኛውም የአካባቢ አካላት መልቀቅ የተከለከለ ነው፡፡ ከቆዳ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች፣ ከቀለም ፋብሪካዎች፣ ከዘይት ፋብሪካዎች፣ ከፓስታ ፋብሪካዎች፣ ከህጻናት ምግብ ቀማሚ ፋብሪካዎች፣ ከጎማ ፋብሪካዎች፣ ከስጋ ማቀነባበሪያዎች፣ከጨርቃጨርቅ፣ከፕላስቲክ፣ከመድኃኒት፤ፋብሪካዎችና ከመሳሰሉትና ሌሎች የተለያዩ ፋብሪካዎችን የሚወጡ ፍሳሻ ቆሻሻዎች የፍሳሽ ዓይነት እንደ ፋብሪካው ዓይነት የተለያየ ስለሆነና የወጣውም ደረጃ በዚሁ መሰረት ስለሆነ

በደረጃው በሰፈረው መስፈርት መሰረት መድረስ የሚገባቸው ደረጃ ከመድረሳቸው በፊት መለቀቅ የለባቸውም፡፡

### 2.4.3. ከጤና ተቋማት የሚወጣ ፍሳሽ ቆሻሻ

የጤና ተቋማት ሆስፒታሎችን፣ የጤና ጣቢያዎችን፣ ከፍተኛና መካከለኛ ክሊኒኮችንና የጤና ኮሌጆችን የሚያጠቃልል ነው፡፡ ከነዚህ ተቋማት የሚወጣ ፍሳሽ ቆሻሻዎች በአብዛኛው በሽታ አስተላላፊ ህዋሳትን ተሸካሚ እንዲሁም የተለያዩ በካይ ኬሚካሎችን የያዙ ስለሚሆኑ በተገቢው መንገድ ሳይታከሙ ወደ አካባቢ መለቀቅ የለባቸውም፡፡

### 2.4.4. ከነዳጅ ማደያዎችና ከጋራዦች የሚወጡ ፍሳሽ ቆሻሻዎች

ከላይ ከተጠቀሱት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚፈጠሩ ፍሳሽ ቆሻሻዎች በውስጣቸው የተቃጠለ ዘይት ግሪስ እና ሌሎች ኬሚካሎችን የያዙ ስለሆኑ በጥንቃቄ ሊያዙ የሚገባቸውና እነዚህ በካይ ነገሮች ከውሃው ሳይለዩ ወደ አካባቢ መልቀቅ በህግ የተከለከለ ነው፡፡ የመኪና ማጠቢያ ፍሳሽ ሳይጣራ ወደ ማንኛውም የአካባቢ ክፍል መልቀቅ ክልክል ነው፡፡ ከነዚህ አገልግሎት መስጫ ተቋማት የሚወገደውን የተቃጠለ ዘይት በተመለከተ በመሬት ላይ መድፋት ፈጽሞ የተከለከለ ሲሆን የተቃጠለ ዘይት ክዳን ባለው ፕላስቲክ  ማጠራቀምና መያዝ አለበት፡፡ ምግብና መጠጥ ይዞ በቆየ ፕላስቲክ ማጠራቀምና መያዝ የተከለከለ ነው፡፡ የተቃጠለ ዘይት መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል የሚቻል ስለሆነ ለመልሶ ተጠቃሚዎችም ማስረከብ የሚገባ ሲሆን መልሶ ተጠቃሚዎች አካባቢን፣ አየርንና ውሃን በማይበክል መልኩ መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡

### 2.4.5. ከንግድ ተቋማት የሚወጣ ፍሳሽ ቆሻሻ

በንግዱ ህብረተሰብ አካባቢ በተለያየ ሁኔታ የሚጠራቀም ጊዜያቸው ያለፈባቸው ፈሳሽ ኬሚካሎች የሚኖሩ ሲሆን የእነዚህም አያያዝ በጥንቃቄ ሊሆን ይገባል፡፡ አደገኛ የሆኑ ፈሳሽ ኬሚካሎች በፕላስቲክ መያዣ መጠራቀም የሚገባቸው ሲሆን ይህም በቀዝቃዛ ቦታ ክዳን ባለው መያዣ እንዲሁም በተዘጋጀላቸው ቀዝቃዛና በሲሚንቶ በተለሰነ ቦታ እስከሚወገዱ ድረስ አንዱ ኬሚካል ከሌላኛው በማይነካካበትና በማይቀላቀልበት መንገድ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡ ሌሎቹም ጥቅም ላይ መዋል የማይችሉና አደገኛ ያልሆኑም ኬሚካሎች ቢሆኑ በተገቢው መንገድ ተይዘው መወገድ በሚገባቸው መንገድ በባለሙያ በመታገዝ ወደ አካባቢ ደረጃ

ከመጡ በኋላ ማስወገድ ይገባል፡፡ ከዚህ ውጭ ግን በመንገድ ዳር ወይም በቱቦ ውስጥ ወይም በአፈር ላይ ወይም ወደ አየር ወይም ወደ ውሃ አካላት መልቀቅ የተከለከለ ነው፡፡

### 2.5. አየር ብክለት

ሀ.ከኢንዱስትሪ፣ ከሃይል ማመንጫ፣ ከተሽከርካሪዎች፣ ከአደገኛ ነገሮች፣ ከአምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማትና ከመሳሰሉት የሚመነጩ አየር የሚበክሉ የበካይ ነገሮች ብናኝ/ጭስ/ ክርፋት ወይም ሽታ መጠን በአካባቢው ከሚፈቀደው ደረጃ በላይ መሆን የለበትም፡፡

ለ. ፈቃድ ካልተሰጠ በስተቀር ማንኛዉም ሰዉ ለአየር ከወጣለት የጥራት ደረጃ በላይ በካይ ነገሮች ብናኝ፣ ጭስ፣ ሽታና የመሳሰሉት ነገሮች ወደ አካባቢ አየር መልቀቅ ክልክል ነዉ፡፡

ሐ.ቆሻሻ በሚቃጠልበት ጊዜ ሌሎች በካዮች ይፈጠራሉ እነሱም ካርቦን ዳይ-ኦክሳይድ፣ ካርቦን ሞኖ-ኦክሳይድ ናይትሮጅን-ዳይኦክሳይድ የመሳሰሉት እና ብናኝ በካዮች ይፈጠራሉ ስለዚህ ቆሻሻ ሲቃጠል የሚወጣዉ ጭስ አየርን በመመረዝ ለብክለት መንስኤ ስለሚሆን ከኢንዱስትሪ፣ ከሃይል ማመንጫ፣ ከመኖርያ ቤት፣ ከአምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች እንዲሁም ቁሳቁሶች ሜዳ ላይ ማቃጠል የተከለከለ ነው፡፡

### 2.6. የእይታ ብክለት

ሀ. ፈቃድ ካልተሰጠ በስተቀር ማንኛዉም ሰዉ እይታን ከተፈቀደ የምልከታ ደረጃ በላይ በካይ ነገሮች ብናኝ፣ ጭስ ፣የመሳሰሉት ነገሮች አካባቢ መበከል፣ ጉዳት ማድረስ ክልክል ነዉ፡፡

ለ. በልማት ምክንያት ለህንጻ ስራ፣ ለመንገድ ስራ፣ ለማስታወቂያ ስራ ተብሎ የሚቀመጥ ማንኛውም አንጸባራቂ ነገር በሰውና በአካባቢ ላይ ጉዳት ~~የሚያደርስ~~ ሊያደርስ በሚችል መልኩ መጠቀም ወይም ማስቀመጥ መስቀል የተከለከለ ነው፡፡

# ክፍል አራት

## 3. የብክለት ቁጥጥር መነሻዎች

### 3.1. ጥቆማ

### 3.2. አቤቱታ

### 3.3. ጥቆማ

ሀ. ማንኛውም ሰው ማንኛውም ዓይነት የአካባቢ ብክለት መድረሱን ከአወቀ ወይም ይደርሳል ብሎ ከገመተ ለኮሚሽን መ/ቤቱ ወይም በየደረጃው ለሚገኙ የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ፅ/ቤቶች በሚያመቸው የመገናኛ ዘዴዎች ወይም በአካል ቀርቦ ጥቆማውን ሊያቀርብ ይችላል፡፡

ለ. ጠቋሚው በካዩ ነገር የተለቀቀበትን ወይም በካይ ነገር ሊለቀቅበት ይችላል ብሎ የገመተውን አካባቢክ/ከተማውን፣ ወረዳውን፣ ቀጠናዉንና የአካባቢውን ልዩ ስም ከተቻለም በካይ ነገሩን የለቀቀውን ወይም ሊለቅ ይችላል ብሎ ያሰበውን አካል ወይም ግለሰብ ስም መግለጽ ይኖርበታል፡፡

ሐ. ጠቋሚው በሰጠው ጥቆማ የተወሰደውን የማስተካከያ እርምጃ የመጠየቅና የማወቅ መብት አለው፡፡

መ. ጠቋሚው ለሰጠው ጥቆማ ማስረጃ እንዲያቀርብ አይገደድም፡፡

ሠ. ጠቋሚው ካልፈቀደ በስተቀር ስሙንና አድራሻውን እንዲገልጽ አይገደድም፤ ስሙ እንዳይገለጽ ካሳወቀም ፈቃደኛ ካልሆነ የጠቋሚው ስም በሚስጥር ይያዛል፡፡

#### 3.3.1. አቤቱታ

ሀ. ማንኛውም ሰው በሚኖርበት ወይም በሚሰራበት ወይም በሚዝናናበት ወይም ሌሎች ማህበራዊ ተግባራትን በሚፈጽምበት ወይም በሚንቀሳቀስበት አካባቢ የደረሰ የአካባቢ ብክለት እንዲወገድለት በጋራም ሆነ በተናጠል ለኮሚሽን መ/ቤት ወይም በየደረጃው ለሚገኝ የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ጽ/ቤት መ/ቤቶች አቤቱታ በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

ለ. የአካባቢ ብክለት መድረስ አለመድረሱ ባይረጋገጥም አካባቢን ሊበክል ይችላል ተብሎ የሚገመት የበካይ ነገር ልቀት መኖሩን ከአወቀ፣ ወይም አካባቢን ሊበክል

ይችላል ተብሎ የሚገመት በካይ ነገር ሊለቀቅ ይችላል ብሎ ከገመተ አቤቱታውን ማቅረብ ይችላል፡፡

ሐ. በጽሁፍ የሚቀርብ አቤቱታ በካይ ነገሩ የተለቀቀበትን አካባቢ ክፍለ ከተማውን፣ ወረዳውን፣ ቀጠናውን እንዲሁም ልዩ ቦታውን ስም በካይ ነገሩ መለቀቅ የጀመረበት ጊዜ፣ የሚለቀቀውን የበካይ ነገር ዓይነት፣ የሚለቀቅበትን ወቅት፣ የሚቻል ከሆነም ብክለቱ ያደረሰውን ጉዳት በዝርዝር ማካተት አለበት፡፡

መ. አቤቱታ የሚቀርብበት ቅጽ ኮሚሽን መ/ቤቱ ያዘጋጃል ሆኖም አቤቱታ አቅራቢው በመሰለው መንገድ በጽሁፍ አቤቱታውን ሊያቀርብ ይችላል፡፡

ሠ. አቤቱታ አቅራቢው የሚያቀርበው ቅሬታ በወረቀት ከሆነ በአቤቱታው ላይ መፈረም ይኖርበታል፤

ረ. አቤቱታ አቅራቢው የአቀረበውን አቤቱታ ባቀረበበት መንገድ አፈጻጸሙን የመከታተልና ውጤቱንም የማወቅ መብት አለው፡፡

## 3.4. የብክለት ቁጥጥርና ክትትል ስርዓት

### 3.4.1. መደበኛ እና ድንገተኛ ኢንስፔክሽን ወይም ክትትልና ቁጥጥር ቢባል ምክንያቱም ይህን ከአቤቱታና ጥቆማ ሌላ የብክለት ቁጥጥር መነሻ ስለሆነ፡፡.

ሀ. በመ/ቤቱ የተመደቡ የአካባቢ ብክለት ኢንስፔክተሮች ማንኛውንም ማምረቻ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም በማንኛውም ጊዜ ከአካባቢ ብክለት ጋር በተያያዘ ሁኔታ ቁጥጥርና ክትትል ያደርጋሉ፡፡

ለ. የአካባቢ ብክለት ሊያደርሱ ይችላሉ ተብለው በሚገመቱ ማምረቻ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ መደበኛ የቁጥጥርና የክትትል ፕሮግራም በማውጣት ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

ሐ. ከላይ በ4.1.1 እስከ 4.2.1 ኮሚሽኑ ለስራው ተግባራዊነት የተጠቀሱት ክዋኔዎች በከተማው አስተዳደሩ ስር ለሚገኙ የክፍለ ከተማ ወረዳ መዋቅሮች ላይም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል አምስት

# 4. የቁጥጥርና ምርመራ ስርዓት

## 4.1. ተቆጣጣሪው የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር በሚያደርግበት ጊዜ ሊያሟላቸው የሚገቡ ሁኔታዎች

ሀ. የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር ለማድረግ ተቆጣጣሪው ሲንቀሳቀስ የአካባቢ ብክለት ተቆጣጣሪ ስለመሆኑ ከኮሚሽን መ/ቤት ወይም በየደረጃው ከሚገኝ የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ፅ/ቤቶች የተሰጠ መታወቂያ መያዝና ቁጥጥር ለሚደረግበት አካል የማሳየት ግዴታ አለበት፡፡

ለ. ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋም ወይም ድርጅት ከሚጠቀመው ግብዓት ወይም ምርት አንጻር ልዩ ጥንቃቄ የሚፈልግ ሲሆንና ግብዓቱ በተቀመጠበት ወይም የምርት ሂደት በሚከናወንበት ስፍራ ገብቶ ቁጥጥርና ምርመራ ለማድረግ የተለዩ አልባሳት፣ ጫማና ጓንት ማድረግ አስፈላጊ ከሆነ ተቆጣጣሪው ይህንኑ አሟልቶ መገኘት ወይም ተቋሙ ወይም ድርጅቱ ያዘጋጀውን መጠቀም ይኖርበታል፡፡

ሐ. ተቆጣጣሪው ለስራው አፈጻጸም ደህንነትና መሳካት አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው የፖሊስ አባላት፣ የሰላምና ፀጥታ ጽ/ቤት ሰራተኞች፣ ሙያተኞችንና ሌሎች አጋዥ ሰራተኞችን ይዞ የቁጥጥርና ምርመራ ስራውን ሊያከናውን ይቻላል፡፡

## 4.2. ቁጥጥርና ምርመራ ስለማድረግ

ሀ. ተቆጣጣሪው መደበኛ የቁጥጥር ፕሮግራም በማውጣት ወይም ድንገተኛ የቁጥጥር ስልት በመቀየስ የስራ ባህሪው በአካባቢ ላይ ብክለትን እንዲሁም በሰው ልጅ አኗኗር፣ ጤንነት እና ደህንነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያደርሱ ይችላሉ ተብለው በሚገመቱ ተቋማት ወይም ድርጅት ወይም ሊበከሉ ይችላሉ ተብለው በሚገመቱ የአካባቢ ክፍሎች ላይ በማንኛውም ቀንና ሰዓት ቁጥጥርና ምርመራ ያደርጋል፡፡

ለ. ተቆጣጣሪው ቁጥጥርና ምርመራ በሚያካሂድበት ወቅት ተቋሙ ወይም ድርጅቱ መደበኛ ስራውን በተለመደው አኳኋን ማካሄድ ይኖርበታል፡፡ ሆኖም ግን ቁጥጥርና ምርምራ በሚካሄድበት ወቅት ተቋሙ ወይም ድርጅቱ ስራ አቁሞ ወይም ማሽን ቀዝቅዞ ከሆነ እና የማሽኑ መነሳት ለቁጥጥሩ ስራ አስፈላጊ መሆኑን ተቆጣጣሪው ካመነበት ማሽኑ እንዲነሳ መደረግ አለበት፡፡

ሐ. ተቆጣጣሪው ቁጥጥርና ምርመራ ካደረገ በኋላ ተቋሙ ወይም ድርጅቱ ያለበትን ሁኔታ ገምግሞ የአካባቢ ብክለት ከደረጃ በላይ እያደረሰ መሆን አለመሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ይህ ሁኔታም ለተቋሙ ወይም ለድርጅቱ በጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ከማስተካከያ ሀሳብ ጋር ይገለጽለታል፤ ቁጥጥሩ የተደረገው በአቤቱታ መነሻነት ከሆነ የዚሁ ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡

መ. ቁጥጥርና ምርምራ በሚደረግበት ወቅት ቁጥር ከሚደረግበት ተቋም ወይም ድርጅት የመነጨ አካባቢን ሊበክል ወይም የአካባቢን ንጽህና ሊያጓድል የሚችል ማንኛውም ዓይነት ቆሻሻ በአካባቢ ተዘርክርኮ ወይም እየፈሰሰ ከተገኘ ወይም መጥፎ ሽታ ወይም ጭስ ወይም ብናኝ ነገር ወይም በሌላ ብክለት በተገቢው ሳይያዝ ተለቆ በተቆጣጣሪው ከታዩ በካይ ነገር ወደ አካባቢው እንደተለቀቀ ከተረጋገጠ አስፈላጊው አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰዳል፡፡

### 4.3. ናሙና ለምርመራ ስለመውሰድ

ሀ. የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር በሚደረግበት ወቅት ማንኛውም የአካባቢ ብክለት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ናሙና መውሰድ ካስፈለገ ከተቋሙ ወይም ድርጅቱ ግብዓት ወይም ምርት ወይም ውጋጅ ላይ ለምርመራ በቂ የሆነ ናሙና ተቆጣጣሪው በማንኛውም ድንገተኛ ሰዓት ያለ ክፍያ ሊወስድ ይችላል፡፡

ለ. ናሙናው ሲወሰድ የተቋሙ ወይም የድርጅቱ ኃላፊ ወይም ተወካይ መገኘት ይኖርበታል፡፡

ሐ. በናሙና አወሳሰድ ወቅት የድርጅቱ ኃላፊ ወይም ተወካይ ካልተገኙ ወይም ፈቃደኛ ካልሆኑ የተቆጣጣሪ መ/ቤቱ ባለሙያዎች በጋራ የሚወስዱት ናሙና ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

# ክፍል ስድስት

## 5. መዋቅራዊ የሥራ ክፍፍል

### 5.1. የሥራ ክፍፍል መነሻዎች

### 5.2. የስራ ክፍፍል

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን በማዕከልና በየደረጃው ባሉ ተቋማት ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግባቸው አምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ዝርዝር የሚከተሉት ናቸው፡፡

#### 5.2.1. በማዕከል ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግባቸው የማምረቻና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት/ድርጅቶች ዝርዝር፡፡

6.2.1.1. የእርድ አገልግሎት መስጫ (ቄራዎች)

6.2.1.2. የቆዳ ፋብሪካዎች እና የቆዳ መጋዘን

6.2.1.3. የጨርቃጨርቅ ድርጅቶች

6.2.1.4. የልብስ ስፌት ፋብሪካዎች (ከ100 በላይ የሰው ኃይል ያለው)

6.2.1.5. የጋዝ ማምረቻ ፋብሪካዎች (ከ50 በላይ የሰው ኃይል ያለው)

6.2.1.6. የቀለም ፋብሪካዎች

6.2.1.7. የለስላሳ መጠጥ ፋብሪካዎች

6.2.1.8. የአልኮል መጠጥ ፋብሪካዎች

6.2.1.9. ፎም ፋብሪካዎች

6.2.1.10. የሚስማር ፋብሪካዎች(ከ100 በላይ የሰው ኃይል ያለው)

6.2.1.11. የቆርቆሮ ፋብሪካዎች

6.2.1.12. የወተትና የወተት ተዋፅዖ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች

6.2.1.13. ሆስፒታሎች

6.2.1.14. የመድኃኒት ፋብሪካዎች

6.2.1.15. የእምነ-በረድ ፋብሪካዎች

6.2.1.16. ባለ ኮከብ ሆቴል ቤቶች (3 እና ከዚያ በላይ)

6.2.1.17. ትላልቅ የዘይት ፋብሪካዎች(ከ50 በላይ የሰው ኃይል ያለው)

6.2.1.18. የምግብ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች (ከ30 በላይ የሰው ኃይል ያለው)

6.2.1.19. ጠርሙስና ብርጭቆ ፋብሪካዎች

6.2.1.20. ሳሙናና ዲተርጀንት ፋብሪካዎች (ከ100 በላይ የሰው ኃይል ያለው)

6.2.1.21. የአሉሚኒየምና ብረታ-ብረት ማቅለጫ ፋብሪካዎች

6.2.1.22. ከፍተኛ የምሽት ክበባት ሆኖ ባንድ ያለው ሆቴል፣ ባርና ሬስቶራንት፣ ባር፣ ግሮሰሪ

6.2.1.23. የኬሚካልና አደገኛ ቁሶች ንግድ እና ማምረቻ

6.2.1.24. የኤሌክትሮኒክስ መገጣጠሚያ ፋብሪካዎች (ከ10 በላይ የሰው ኃይል ያለው)

6.2.1.25. የጎማ ፋብሪካዎች

6.2.1.26. ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት (ዩኒቨርሲቲ)

6.2.1.27. ማተሚያ ድርጅቶች (ከ50 በላይ የሰው ኃይል ያለው)

6.2.1.28. የቶነርና ካርቲሬጅ ማምረቻ ፋብሪካዎች

6.2.1.29. ከፍተኛ የፕላስቲክ ማምረቻ ፋብሪካዎች(ከ30 በላይ የሰው ኃይል ያለው)

6.2.1.30. ቡና ማቀነባበሪያ እና እህል ማበጠሪያና ማከማቻ(ከ15 በላይ የሰው ኃይል ያለው)

6.2.1.31. የሃይማኖት ተቋማት ክትትልና ቁጥጥር ላይ እርምጃ መውሰድ

6.2.1.32. የአስፋልት ሬንጅ መደባለቂያ እና ክሬሸር

6.2.1.33. ሌሎች ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸው ፋብሪካዎች

### 5.2.2. በክፍለ-ከተማ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግባቸው የማምረቻና አገልሎት ሰጪ ተቋማት/ድርጅቶች ዝርዝር፡፡

5.2.2.1. ፕላስቲክ ፋብሪካዎች(ከ30 በታች የሰው ኃይል ያለው)

5.2.2.2. የብረታ-ብረትና ኢንጂነሪንግ(መገጣጠሚያ ቶርኖ)

5.2.2.3. የልብስ ስፌት ፋብሪካዎች (ከ30-100 የሰው ኃይል ያለው)

5.2.2.4. የጋዝ ማምረቻ ፋብሪካዎች (ከ50 በታች የሰው ኃይል ያለው)

5.2.2.5. የሚስማር ፋብሪካዎች (ከ100 በታች የሰው ኃይል ያለው)

5.2.2.6. የዘይት ፋብሪካዎች (ከ11- 50 የሰው ኃይል ያለው)

5.2.2.7. የምግብ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች (ከ30 በታች የሰው ኃይል ያለው)

5.2.2.8. ሳሙናና ዲተርጀንት ፋብሪካዎች (ከ100 በታች የሰው ኃይል ያለው)

5.2.2.9. የኤሌክትሮኒክስ መገጣጠሚያ ፋብሪካዎች (ከ10 በታች የሰው ኃይል ያለው)

5.2.2.10. ማተሚያ ድርጅቶች (ከ5- 50 የሰው ኃይል ያለው)

5.2.2.11. ቡና ማቀነባበሪያ እና እህል ማበጠሪያና ማከማቻ (ከ15 በታች የሰው ኃይል ያለው)

5.2.2.12. የዱቄት ፋብሪካዎች

5.2.2.13. የጣውላ መሰንጠቂያ፣

5.2.2.14. የእንጨት ስራ ድርጅቶች

5.2.2.15. የከረሜላ ፋብሪካዎች

5.2.2.16. ሻማ ፋብሪካዎች

5.2.2.17. ሰም ፋብሪካዎች

5.2.2.18. የመስታዎት ስራ

5.2.2.19. የአልሙኒየም መቁረጫ ስ

5.2.2.20. የጥራጥሬና የቅባት እህል ማበጠሪያ

5.2.2.21. የምግብ ማደራጃ

5.2.2.22. የመልሶ መጠቀም ስራ ድርጅቶች (ሪሳይክለሮች)

5.2.2.23. የእንስሳት ገበያና መቆያ በረት

5.2.2.24. የዶሮ እርባታ

5.2.2.25. የቤት እንስሳት ማድለቢያና እርባታ

5.2.2.26. የንብ እርባታ

5.2.2.27. የትላልቅና ቀላል ተሽከርካሪዎች ጥገና ማዕከላት

5.2.2.28. የቅባትና ጥራጥሬ እህሎችን ማበጠሪያና ማከማቻ

5.2.2.29. አነስተኛና መለስተኛ የአሉሙኒየም ማቅለጫና ሞልድ ስራዎች

5.2.2.30. የቆዳና ፕላስቲክ ጫማ ማምረቻ

5.2.2.31. የተሽከርካሪ መገጣጠሚያና ሰርቪስ መስጫ ማዕከላት

5.2.2.32. የትላልቅና ቀላል ተሽከርካሪዎች ጥገና ማዕከላት

5.2.2.33. ከ3 ኮከብ በታች ሆቴሎች

5.2.2.34. የትምህርት ተቋማት(ኮሌጆች)

5.2.2.35. የጤና ተቋማት (ጤና ጣቢያዎች)

5.2.2.36. የወርቅና ጌጣጌጥ ሥራዎች

5.2.2.37. የድርና ማግ ማንጣትና ማቅለሚያ

5.2.2.38. ክፍተኛ የምሽት ክበባት ሆኖ ሞንታርቦ ያለው/ ሆቴል፣ ባርና ሬስቶራንት፣ ባር፣ ግሮሰሪ

5.2.2.39. ኮስሞቲክስ ማምረቻ

5.2.2.40. ጣውላና ኮምፐርሳቶ እንዲሁም ሌሌች የደን ውጤቶችን ማስመጣት፣ ማከማቸትና ማከፋፈል፡፡

5.2.2.41. የብረታ-ብረትና የእንጨት ስራ ማዕከላት

5.2.2.42. ቦሮንዳዮ ብክለት ክትትል

5.2.2.43. የስፖንጅ ውጤቶች ማምረት

5.2.2.44. የሃይማኖት ተቋማት ክትትልና ቁጥጥር

5.2.2.45. ሌሎች ባህርያቸው ተመሳሳይ የሆኑና በአካባቢ ላይ ብክለት ያላቸው ድርጅቶችና ተቋማት፤

### 5.2.3. በወረዳ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግባቸው የማምረቻና አገልሎት ሰጪ ተቋማት/ድርጅቶች ዝርዝር፡፡

5.2.3.1. የትምህርት ተቋማት (አንደኛ፣ ሁለተኛና መሰናዶ ት/ቤቶች)
5.2.3.2. የጤና ተቋማት (ክሊኒኮች)
5.2.3.3. ኮከብ አልባ ሆቴሎች፣ ምግብ ቤቶችና ሬስቶራንቶች
5.2.3.4. ወፍጮ ቤቶች
5.2.3.5. የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቦታዎች
5.2.3.6. ፕላስቲክ ፋብሪካዎች (ከ10 በታች የሰው ኃይል ያለው)
5.2.3.7. የልብስ ስፌት ፋብሪካዎች (ከ30 በታች የሰው ኃይል ያለው)
5.2.3.8. ሳሙናና ዲተርጀንት ፋብሪካዎች (ከ30 በታች የሰው ኃይል ያለው)
5.2.3.9. ማተሚያ ድርጅቶች/ከ5 በታች የሰው ኃይል ያለው/
5.2.3.10. ዳቦና ኬክ ማምረቻዎች
5.2.3.11. አነስተኛ የምግብ ማቀነባበሪያዎች
5.2.3.12. የዘይት ፋብሪካዎች / ከ10 በታች የሰው ኃይል ያለ
5.2.3.13. ፎቶ ስቱዲዮዎች
5.2.3.14. ግሮሰሪና ምግብ ቤቶች በስፒከር የሚሰራ
5.2.3.15. ጎሚስታዎች
5.2.3.16. የገላ መታጠቢያ ቤቶች
5.2.3.17. የልብስ እጥበት (ላውንደሪ) አገልግሎት ሰጪዎች
5.2.3.18. የቤት ውስጥ ምግብ ማቀነባበሪያዎች
5.2.3.19. ቪዲዮና ሙዚቃ ቤቶች
5.2.3.20. ቡና መቂያ፣ መፍጫ፣ ማለስለሻ፣ ማከማቻና ማከፋፈያ ቤቶች
5.2.3.21. የእምነ-በረድ መቁረጫ፣ ማለስለሻ፣ ማከማቻና ማከፋፈያ ቤቶች
5.2.3.22. የጣውላ መሰንጠቂያ፣ ማለስለሻ፣ ማከማቻና ማከፋፈያ ቤቶች
5.2.3.23. የመኪና እጥበትና ነዳጅ ማደያ ቁጥጥር
5.2.3.24. ብሎኬትና ቱቦ ማምረቻ

5.2.3.25. የማግኒዥየም ቦርድ ስራ

5.2.3.26. ጠጅና አረቄ ቤቶች

5.2.3.27. ድምጽ የሚያመነጩ ሱቅና ቡቲክ ቤቶች

5.2.3.28. ታፕሰሪ

5.2.3.29. ቆሎ የሚሰሩ

5.2.3.30. ስሚንቶ እና ጅብሰም ማከማቻ፤መጋዘን

5.2.3.31. የአትክልትና ፍራፍሬ መሸጫ ቦታዎች

5.2.3.32. የሃይማኖት ተቋማት ክትትልና ቁጥጥር

5.2.3.33. ሌሎች ባህርያቸው ተመሳሳይ የሆኑና በአካባቢ ላይ ብክለት ያላቸው ድርጅቶችና ተቋማት፤

## 5.3. የስራ ክፍፍል አተገባበሩን በተመለከተ

ሀ. ከላይ በክፍል ስድስት በ5.2.በማዕከል፣ በክ/ከተማ እና በወረዳ የተደረገው የስራ ክፍፍል እንደተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን በሚመለከተው አካል ሳይፈታ ቀርቶ በአቤቱታ ሆነ በጥቆማ ጉዳዩ ወደ ሚቀጥለው መዋቅር ከመጣ ያለምንም ክልከላ ማዕከል ወደ ክ/ከተማ እና ወረዳ እንዲሁም ክ/ከተማ ወደ ወረዳ ወርዶ ችግሩን ይፈታል፡፡

ለ. ወረዳ ላይ የተሟላ ባለሙያ ከሌለ ክ/ከተማው የራሱ ስራ ድርሻ ላይ ደርቦ ያከናውናል፡፡

ሐ. በክ/ከተማ ላይ የተሟላ ባለሙያ ከሌለ በማዕከል ባለው ስራ ድርሻ ላይ ደርቦ ያከናውናል፡፡

መ. ኮሚሽኑ ክ/ከተሞችና ወረዳዎች እንዲሁም ክ/ከተሞች በሥራቸዉ ያሉ የወረዳ ጽ/ቤቶች ይህን ስለመፈጸማቸዉ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋሉ፡፡

ሠ. ከማዕከል እስከ ወረዳ ያሉ መዋቅሮች የሚሰሯቸውን ስራዎች በሪፖርት፣ የሚወስዷቸውን እርምጃዎች ደግሞ በግልባጭ ማሳወቅ አለባቸው፡፡

# ክፍል ሰባት

## 6. የአካባቢ ብክለትን ለማረም መወሰድ የሚገባው አስተዳደራዊ እርምጃ

### 6.1. የበካይ ነገሮች ልቀቱን ማስቆም

ማንኛውም አገልግሎት ሰጭ ተቋም ወይም የማምረቻ ድርጅት ተገቢውን የውጋጅ ልቀት ፈቃድ ሳይዝ ማንኛውንም ዓይነት በካይ ነገር ወይም የአካባቢን ጽዳትና ደህንነት ሊያጓድል የሚችል ውጋጅ ወደ የትኛውም የአካባቢ ክፍል ለቆ ከተገኘ፡-

ሀ. ልቀቱን በማስጠንቀቂያ በተገለፀው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲያቆም ተቆጣጣሪው የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡

ለ. ያላግባብ ያከማቸውን ወይም በየቦታው አዝረክርኮ ያስቀመጠውን ደረቅም ሆነ ፍሳሽ ቆሻሻ ከላይ በተራ ቁጥር6.1.ሀ.መሰረት በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ካለቀ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ በማስወገድ ለሚመለከተው የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽንና ፅ/ቤቶች ሪፖርት ያደርጋል፡፡

ሐ. በተራ ቁጥር6.1.ንዑስ ቁጥር ሀ እና ለ መሰረት ካልተፈጸመ ወይም በካዩን ነገር በለቀቀው አካል ተቆጣጣሪው ሊስማማበት የሚችል ሌላ አማራጭ ሀሳብ ካልቀረበ ድርጅቱ ወይም ተቋሙ እንዲታሸግ ተቆጣጣሪው የውሳኔ ሃሳብ ለበላይ ኃላፊ ያቀርባል፡፡

መ. ኮሚሽኑ ወይም በስሩ ያሉ ጽ/ቤቶች የድርጅቱን ወይም የተቋሙን መታሸግ አግባብ ሆኖ ካገኙት ከአምስት ቀን እስከ ሦስት ወር እንዲታሸግ ይወስናል፤

ሠ.የኮሚሽኑ ውሳኔ ድርጅቱ ወይም ተቋሙ የሚዘጋበትን ቀንና ታሽጎ የሚቆይበትን ጊዜ በመግለፅ ለሚታሸገው ድርጅት ወይም ተቋም እንዲደርስ ይደረጋል፤ እንደዚሁም የውሳኔው ግልባጭ ለፈቃድ ሰጪ መ/ቤቶችና ሌሎች አግባብነት ላላቸው መ/ቤቶች እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

ረ. ድርጅቱ ወይም ተቋሙ ከመዘጋቱ በፊት እንደ ችግሩ አሳሳቢነት የቅድመ ዝግጅት ጊዜ እንዲኖረው ከ12 ሰዓት እስከ 48 ሰዓት ጊዜ በጽሑፍ እንዲደርሰዉ ይደረጋል ፡፡

ሰ. እሸጋ ገንጥሎ(ተደብቆ) ሲሰራ የተገኘ ድርጅት ወይም ተቋም የኮሚሽኑን ውሳኔ ባለማክበሩ ድርጅቱ ወይም ተቋሙ ለተጨማሪ ሁለት ወር ተዘግቶ እንዲቆይ ይደረጋል፡፡ ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ህጋዊ እርምጃዎች ይወሰዳል፡፡

### 6.2. የተዘጋው ድርጅት ወይም ተቋም የሚከፈትበት አገባብ

ሀ. በአካባቢ ብክለት በማድረሱ ወይም ብክለት ሊያደርሱ የሚችሉ ነገሮችን ወደ አካባቢ በመልቀቁና እንዲያስተካክል በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ሣያስተካክል በመቅረቱ ምክንያት በኮሚሽኑ ውሳኔ የተዘጋ ድርጅት ወይም ተቋም የኮሚሽኑን ውሳኔ አክብሮ ድርጅቱን ወይም ተቋሙን የዘጋና የበካይ ነገሮች ልቀቱን ሊያስወግድ የሚችል ቴክኖሎጂን በመጠቀም /የአሰራር/ ማሻሻያ ካደረገና የለቀቀውን በካይ ነገር ካፀዳ በኋላ የተዘጋው ድርጅት ወይም ተቋም እንዲከፈትለት ለኮሚሽኑ ሲያመለክት የዉዴታ ግዴታ ዉል መግባትና ላደረሰዉ ጥፋት የሚቀጣበት ሁኔታ ይታያል፡፡

ለ. ኮሚሽኑ ማመልከቻው ሲደርሰው በማመልከቻው ላይ የተገለፁት ነገሮች በትክክል የተፈጸሙ ስለመሆናቸው ወደ ቦታው ተቆጣሪዎችን በመላክ በመስክ ሲያረጋግጥ የጊዜ ገደቡ ባያልቅም የተዘጋው ድርጅት ወይም ተቋም እንዲከፈት ውሳኔ ይሰጣል፤ የውሳኔውም ግልባጭ ድርጅቱ ሲዘጋ ግልባጭ የተደረገላቸው መ/ቤቶች ሁሉ እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡

### 6.3. ልዩ ልዩ እርምጃዎች

#### 6.3.1. የአካባቢ ብክለት ጥፋትና ቅጣት

ሀ. የአካባቢ ብክለት ናሙና ከተወሰደ በኋላ ለአካባቢው ከተፈቀደለት ደረጃ በላይ ሆኖ ከተገኘ ለአምራች ድርጅት፣ ለአገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና ለሌሎች ብክለት አመንጪ ለሆኑ አካላት አፋጣኝ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፡፡

ለ. የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው አካል ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው ቀን ጀምሮ ለአገልግሎት ሰጭ ተቋማት ከሶስት(3) ቀናት እና ለአነስተኛና ጥቃቅን እንዲሁም በግል በአነስተኛ ደረጃ የሚያመርቱ የማምረቻ ተቋማት ከሰባት ቀናት(7)ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ብክለቱን በማስቆም፣ ችግሩን ፈትቶ

ማስጠንቀቂያ ለጻፈው ኮሚሽን መ/ቤት ወይም በየመዋቅሩ ላሉ የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ጽ/ቤቶች ያስተካከለበትን መረጃ ሪፖርት በጽሁፍ እና በአካል ማቅረብ አለበት፡፡ ነገር ግን የአምራች ድርጅቶች አሳማኝ ምክንያት ካቀረቡ ጉዳዩ ለኮሚሽን መስሪያ ቤት እና በየመዋቅሩ ላሉ የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ጽ/ቤቶች የበላይ ሃላፊዎች ቀርቦ በግዴታ ውል ተጨማሪ ጊዜ ሊሰጠው ይችላል፡፡

ሐ. የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው አካል ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው ጊዜ ጀምሮ ለኢንዱስትሪዎች እና ለፋብሪካዎች በ1 ወር ጊዜ ውስጥ ብክለቱን በማስቆም፣ ችግሩን ፈትቶ ማስጠንቀቂያ ለጻፈው ኮሚሽን መ/ቤት ወይም በየመዋቅሩ ላሉ የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ጽ/ቤቶች ያስተካከለበትን መረጃ ሪፖርት በጽሁፍ እና በአካል ማቅረብ አለበት፡፡

መ.ድርጅቶቹ አሳማኝ ምክንያት በማቅረቡ ጉዳዩ ለኮሚሽን መስሪያ ቤቱ እና አካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ጽ/ቤት የበላይ ሃላፊዎች ቀርቦ በግዴታ ውል ተጨማሪ ጊዜ ሊሰጠው ይችላል፡፡

ሠ.በ "ሀ" እና "ለ" የተገለፀው ሳይፈፅም ቢቀር፣ ብክለት አድራሹ አካል ላይ ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

መ.ድርጅቶቹ አሳማኝ ምክንያት በማቅረቡ ጉዳዩ ለኮሚሽን መስሪያ ቤቱ እና አካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ጽ/ቤት የበላይ ሃላፊዎች ቀርቦ በግዴታ ውል ተጨማሪ ጊዜ ሊሰጠው ይችላል፡፡

ሠ.በ "ሀ" እና "ለ" የተገለፀው ሳይፈፅም ቢቀር፣ ብክለት አድራሹ አካል ላይ ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

ረ.አንድ የተፈጥሮ ሰው የዚህን መመሪያ በመተላለፍ ወደ አካባቢ በመልቀቅ ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ ከአንድ ሺህ (1000.00) ብር በማያንስና ከአምስት ሺህ (5000.00) ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከአንድ ዓመት በማያንስና ከአስር አመት በማይበልጥ እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡ ጥፋቱን የፈጸመው በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከሆነ ደግሞ ከሃምሳ

ሺ.ህ(50000.00) ብር በማያንስና ከመቶ ሺ.ህ(100000.00) ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

ሰ.የስራ ሀላፊውም ከ5 (አምስት) ዓመት በማያንስና ከ10 (አስር) ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም ከአምስት ሺ.ህ (5000.00) ብር በማያንስና ከአስር ሺ.ህ (10000.00) ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

ሸ. ለሁለተኛ ጊዜ ብክለት አስተካክሎ ከተገኘ ለአገልግሎት ሰጪ ተቋም፣ አነስተኛና ጥቃቅን እንዲሁም በግል በአነስተኛ ደረጃ የሚያመርቱ የማምረቻ ተቋማት ብር ሃያ አምስት ሺ.ህ (2500.00) የገንዘብ መቀጮ እና የውዴታ ግዴታ ስምምነት ፈፅሞ እሺጋው ይነሳለታል፡፡

ቀ.በንዑስ ቁጥር6.4.1.ሀ.ደተጠበቀ ሆኖ፣ አንድ የተፈጥሮ ሰው ብክለቱን ለመጀመሪያ ጊዜ ካደረሰ አንድ ሺ.ህ (1000.00) ብር የገንዘብ መቀጮ እና ውዴታ ግዴታ ስምምነት ይፈፅማል፡፡

በ.ለሁለተኛ ጊዜ ጥፋት ከፈፀመ፣ ከአምስት ሺ.ህ (5000.00) ብር ይቀጣልና ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት እንዲሄድ መደረግ አለበት፡፡

ሰ. ለኢንዱስትሪና ትላልቅ ፋብሪካዎች ብክለቱን ለሁለተኛ ጊዜ ካደረሰ መቶ ሺ.ህ (100000.00) ብር የገንዘብ መቀጮ እና የውዴታ ግዴታ ስምምነት ፈፅሞ እሺጋው ይነሳለታል፡፡

ተ. ማንኛውም ሰዉ ድርጅቱ ወይም ተቋሙ በብክለት ምክንያት የተወሰደውን አስተዳደራዊ እርምጃ ውሳኔ በመተላለፍ የታሸገውን ገንጥሎ ወይም በማንኛውም ሁኔታ ተደብቆ ሲሰራ የተገኘ፣ አግባብነት ባላቸው የወንጀል ህጎች ይጠየቃል፡፡

## 6.4. ከአደገኛ ነገሮች ጋር በተገናኘ ስለሚፈጸሙ ጥፋቶች የሚወሰዱ እርምጃዎች

6.5.1. የሚከተሉትን ድርጊቶች የፈጸመ ማንኛውም ሰው ጥፋተኛ ነው፡፡

ሀ. አደገኛ ጎጅ ቁሶችን ፤ የምርት ሂደትና ቆሻሻ በአግባቡ አለመያዝ፤

ለ. ስለቆሻሻው ወይም ኬሚካሉ ወይም አደገኛ ሂደት ሌሎች ቁሶች ምንነት እያወቀ የተሳሳተ ነገር መጻፍ ፤

ሐ. ስለቆሻሻው ወይም ኬሚካሉ ወይም አደገኛ ድርጊት ወይም ነገር መረጃ መደበቅ ወይም መከልከል፤

መ. ለህገወጥ ቆሻሻው ወይም ኬሚካሉ ወይም አደገኛ ድርጊት ወይም እንቅስቃሴ መተባበር፤

6.5.1.ከላይ የተዘረዘሩትን ጥፋቶች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 መሰረት የሚከተለውን ቅጣት ሊቀጣ ይችላል፡፡

ሀ.ያለ ፈቃድ ሰጭው እውቅና አደገኛ ቆሻሻ ወደ አስተዳደሩ ሲያስገባ የተገኘ ከአምስት አመት ባልበለጠ ጽኑ እስራት እና ከከምስት መቶ ሺህ (500000.00) በማያንስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

ለ.ያለ ፈቃድ ሰጭው እውቅና አደገኛ ቆሻሻ ወደ ሀገር ውስጥ ሲያስገባ የተገኘ በዘጠና (90) ቀናት ውስጥ ወደ መጣበት ሀገር መልሶ ካልወሰደ ወይም ካላስወገደ አምስት አመት ባልበለጠ ጽኑ እስራት እና ከአምስት መቶ ሺህ (500000.00) በማያንስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

ሐ.በህገወጥ መንገድመ ሆነ በህጋዊ መንገድ አደገኛ ቆሻሻ ወደ ሀገር ውስጥ ሲያስገባ አካባቢን የበከለ እንደሆን አስር አመት ባልበለጠ ጽኑ እስራት እና ከከምስት ሚሊዮን (5000000.00) ብር በማያንስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

መ.በህገወጥ መንገድመ ሆነ በህጋዊ መንገድ አደገኛ ቆሻሻ ወደ ሀገር ውስጥ ሲያስገባ አካባቢን የበከለ እንደሆን የተበከለውን አካባቢ ያለከመ እንደሆን ሃያ አመት ባልበለጠ ጽኑ እስራት እና ከአስር ሚሊዮን (10000000.00) ብር በማያንስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

ሠ.ያለ ፈቃድ ሰጭው እውቅና ባልታደሰ ፈቃድ አደገኛ ቆሻሻ ያጓጓዘ፤ ያከማቸ፤ ወይም መልሶ ጥቅም ላይ ያዋለ እንደሆነ ከአምስት አመት ባልበለጠ ጽኑ

እስራት እና ከከምመቶ ሺህ (500000.00) ብር በማያንስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

ረ.ያልታከመ አደገኛ ቆሻሻ ወደ አካባቢ ወይም ወደ ፍሳሽ መስመር በቀጥታ የለቀቀ እንደሆነ፤ የተበከለው አካባቢ የማከም ግዴታው እንደተጠበቀ ሆኖ ከአምስት አመት ባልበለጠ ጽኑ እስራት እና ከአምስት መቶ ሺህ (500000.00) ብር በማያንስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

ሰ. የሀሰት መረጃ በማቅረብም ሆነ በሌላ ማንኛውም መልኩ የተቆጣጣሪውን ስራ ያደናቀፈ እንደሆን፤ ከአምስት አመት ባልበለጠ ጽኑ እስራት እና ከሃምሳ ሺህ (50000.00) ብር በማያንስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

## 6.5. ከተቆጣጣሪዎች ጋር በተያያዘ ስለሚፈጸሙ ጥፋቶች

ሀ.ለብክለት ቁጥጥር የተመደበ ተቆጣጣሪ ስራውን እንዳያከናውን ያደናቀፈ ወይም ያሰናከለ፣ ተቆጣጣሪው በህግ መሰረት የጠየቀውን ወይም ያዘዘውን ያልፈጸመ

ለ.በማስመሰል ተቆጣጠሪ ነው ሊባል የሞከ ወይም ተቆጣጣሪ መስሎ ህብረተሰቡ ላይ ዛቻና ማስፈራሪያ የፈጸመ፤

ሐ.ተቆጣጣሪ ወደ ማንኛውም ቦታ ወይም ቅጥር ግቢ እንዳይገባ ወይም መዛግብት እንዳይመረምር ያደናቀፈ ማንኛውም ወረቀት፤ ማህደር ወይም ሌላ ሰነድ እንዳይፈተሽ፣ እንዳይገለብጥ ወይም ለይቶ እንዳይቀዳ የከለከለ፣ ለተቆጣጣሪ መረጃ የከለከለ፣ ያሳሳተ ወይም የተሳሳተ መረጃ የሰጠ ማንም ሰው ጥፋት ፈጽሟል፡፡

መ. በዚህአንቀጽ6.6. ሀ፤ለ እና ሐ መሰረት ጥፋት የፈጸመ የተፈጥሮ ሰው ጥፋተኝነቱ ሲረጋገጥ ከሶስት ሺህ ብር (3000.00) ብር በማያንስና ከአስር ሺህ (10000.00) ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤ ጥፋቱን የፈጸመ በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከሆነ ደግሞ፣ ጥፋተኝነቱ ሲረጋገጥ ከአስር ሺህ (10000.00) ብር በማያንስና ከሃያ ሽህ (20000.00) ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤ የስራ ኃላፊው ከአንድ ዓመት በማያነስና ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም ከአምስት ሺህ (5000.00) ብር በማያንስና ከአስር ሺህ (10000.00) ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

## 6.6. መዛግብትን በተመለከተ ስለሚፈጸሙ ጥፋቶች

አንድ ሰው በዚህ መመሪያ መሰረት በመዝገብ እንዲሰፍር የተጠየቀውን የእንቅስቃሴ፣ የምርት፣ የቆሻሻ ዓይነት፣ ባህርይ ወይም መጠን ወይም ሌላ ተፈላጊ መረጃ በተገቢው ሳይመዘግብ ከቀረ ወይም በመዝገብ የሰፈረውን ከለወጠ ከአስር ሺህ (10000.00) በማያንስና ከሃያ ሺህ (20000) ብር ማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

## 6.7.በፍትሐ-ብሔር እና በወንጀል ተጠያቂነት

ሀ. ማንኛውም ሰው የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች በመተላለፍ ወይም በመጣስ በአካባቢ ላይ ለሚያደርሰው ብክለት እና በሰዎች ደህንነት አኗኗርና ቁሳዊ ጥቅሞች ላይ በብክለቱ ምክንያት ለሚደርሰው ጉዳት እንደቅደም ተከተሉ፡-

ለ.አካባቢን ከብክለቱ በፊት ወደ ነበረበት ሁኔታ በራሱ ወጭ የመመለስ ግዴታ አለበት፤

ሐ. በሰዎች ደህንነት አኗኗር እና ቁሳዊ ጥቅሞች ላይ ብክለቱ ያደረሰውን ጉዳት የመካስ ሃላፊነት አለበት፤

መ.ከአካባቢ ብክለት ጋር የተገናኘ ጉዳት የቀረበለት የፍትህ ተቋም፣ ዋናውን ጥያቄ እልባት ከመስጠቱ በፊት፣የብክለቱን ድርጊት በካዩ እንዳይጀምር ወይም እንዳይቀጥል ወይም ብክለት ያስከተለው ድርጊት እንዲቆም ትእዛዝ መስጠት አለበት፡፡

## 6.8.ስለወንጀል ኃላፊነት

6.9.1.የአካባቢ ብክለትን ለማረም መወሰድ የሚገባው እርምጃ፣ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የተላለፈ ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት በመመሪያው በተካተተው ዝርዝር መሰረት በሰራው ጥፋት አስተዳደራዊ እና ህጋዊ እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

## 6.9.ንብረት ስለመውረስና ወደነበረበት ሁኔታ ስለመመለስ

6.9.1 ይህንን መመሪያ በመጣስ ጥፋተኝነቱ በተረጋገጠበት ሰዉ ወይም ተቋም ላይ ከሚወሰንበት ማንኛዉም ቅጣት በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ፡-

ሀ. ለጥፋቱ ተግባር የዋለ ማንኛዉም ነገር ተወርሶ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ወይም በሌላ መንግድ እንዲወገድ ይደረጋል፣

ለ. አካባቢዉን ወይም መሳሪያዉን የማፅጃ፣ ኬሚካሉን ወይም እቃዉን የማስወገጃ ወጪ ተከሳሹ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

ሐ. ጉዳት የደረሰበትን አካባቢ ተከሳሹ በራሱ ወጪ ወደነበረበት ሁኔታ እንዲመልስ ወይም ደግሞ የማይቻል ከሆነ ተገቢ ካሳ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

## መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ……ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን

መጋቢት፣ 2013

አዲስ  አበባ